# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

## ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ

17 ኛ ዓመት ቁጥር 94 አሶሳ
መስከረም 2003 ዓ.ም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት
ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ


**አዋጅ ቁጥር ፺፬/፪ሺ፫**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት እና ስልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፺፬/፪ሺ፫**

የክልሉን አስፈጻሚ የመንግስት አካላት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥርን $፮/፲፱፻፺፰ በድጋሚ ማሻሻል በማስፈለጉ፡-

በክልሉ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ውስን የሆነውን የሕዝብና የመንግስት ሀብት ቁጥብ በሆነ አኳኃን ለመጠቀም በሚያስችል አኳኃን የተቀናጀ አስተዳደር እና አገልግሎት በመስጠት ለዘላቂ ልማት እና ድህነትን ለማጥፋት ብሎም ለመልካም አስተዳደር መስፈን የላቀ ድርሻ እንዳለው በመገንዘብ ፡-

እንዲሁም ብቃት ያለውን የማስፈጸም አቅም ለመገንባት ግልጽና ቀልጣፋ በሆነ መዋቅር መተካት አስፈላጊ መሆኑን በማመን በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ #፱/፫.፩ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ *"የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 94/2003ዓ/ም"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩. **"የክልሉ ም/ቤት"** ማለት በተሻሻለዉ የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፮/፩ መሠረት የተቋቋመዉ አካል ነው፡፡

፪. **"ህገ-መንግስት"** ማለት የተሻሻለው የ፲፱፻፺፭ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ነው፡፡

፫. **"የመስተዳድር ምክር ቤት"** የክልሉ የህግ አስፈጻሚ አካል የሆነው የክልል መስተዳድር ም/ቤት ሲሆን እንደነገሩ ሁኔታ የተዋረድ አስፈጻሚ አካላት ሊጨምር ይችላል፡፡

፬. **"ቢሮ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ከፍተኛ የመንግስት አስፈጻሚ አካል እና እንደነገሩ

ሁኔታ ሌሎች መሥሪያ ቤቶችን በበላይነት የሚመራ ነው፡፡

፭. "**ሌሎች መሥሪያ ቤቶች**" ማለት በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጐች መሠረት የተቋቋሙ ወይም የሚቋቋሙ ጽህፈት ቤቶችን፣ ኮሚሽኖችን፣ ባለሥልጣኖችን፣ ተቋማትንና ሌሎች መሰል አስፈጻሚ አካላትን ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ አስፈጻሚ አካላት

### ፫. መቋቋም

የመንግስት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሕጐችን በሥራ ላይ የሚያውሉና አስተዳደራዊ ተግባሮችን የሚያከናውኑ አስፈጻሚ አካላት እንደሚከተለው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡፡

፩. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት,

፪. የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት

፫. የካቢኔ አባል የሆኑ ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች፣

፬. ሌሎች ቢሮዎችና መስሪያ ቤቶች፣

፭. የተዋረድ የዞን ጽ/ቤት ወይም መምሪያዎች ወይም ዴስኮች እና የወረዳ ጽ/ቤቶች፡፡

### ፬. ስለ ክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

፩. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ ፶፱ እና በሌሎች ህጎች ተለይቶ የተመለከተው ይሆናል፡

፪. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የመስተዳድር ምክር ቤትና የርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር ፴፫/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳ እና በደንብ ቁጥር ፳/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፮ ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል፡፡

### ፭. ስለ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር በሕገ መንግስቱ አንቀጽ ፳፩ እና በሌሎች ህጎች ተለይቶ የተመለከተዉ ይሆናል፡፡

### ፮. የብሔረሰብ አስተዳደር ም/ቤት

የብሔረሰብ አስተዳደር ም/ቤት ስልጣንና ተግባር በህገ መንግስቱ አንቀጽ ፸፰ እና በአዋጅ ቁጥር አንቀጽ ፸፫/፳፪ ሥርና በሌሎች ህጎች ተለይቶ የተመለከተው ይሆናል፡፡

### ፯. የተዋረድ የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤቶች

የተዋረድ የወረዳና ቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤቶች ስልጣንና ተግባር በህገ-መንግስቱ አንቀጽ ፺፪ እና ፺፫ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር ፹፯/፳፻፪ ዉስጥ እና በሌሎች ህጎች ተለይቶ የተመለከተው ይሆናል፡፡

፰. **<u>የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት</u>**

፩ የክልል መስተዳድር ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ ርዕሰ-መስተዳድር

ለ/ ምክትል ርዕሰ-መስተዳድር

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፱) ሥር የተመለከቱ ካቢኔ አባላት የሆኑ ቢሮዎች ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች፣

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ሥር ከተመለከቱት ውጭ ርዕሰ መስተዳድሩ የመስተዳድር ም/ቤት አባላት እንዲሆኑ በተለይ የሚመርጣቸው የሌሎች ቢሮዎች ኃላፊዎችና ባለሥልጣናት፣

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ሥር የተመለከተው ማናቸውም የካቢኔ አባል በመስተዳድር ም/ቤቱ ስብሳባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ምክትሉ ወይም ከአንድ በላይ ምክትሎች ካሉት በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ኃላፊ ወይም ሌላ ተወካይ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በምትክ አባልነት ይሳተፋል፡፡

፱. **<u>መስተዳድር ምክር ቤት /የካቢኔ/ አባል የሆኑ ቢሮዎችንና ጽ/ቤቶችን እንደገና ስለማቋቋም</u>**

የሚከተሉት የመስተዳድር ም/ቤት አባል የሆኑ ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁመዋል፡፡

፩ የአቅም ግንባታና ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ፣

፪ የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፣

፫ የንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርትና ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ፣

፬ የአስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ፣

፭ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት፣

፮ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣

፯ የውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ፣

፰ የጤና ጥበቃ ቢሮ፣

፱ የፍትህ ቢሮ፣

፲ የትምህርት ቢሮ፣

፲፩ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት፣

፲፪ የሴቶች፣ የወጣቶችና የህፃናት ጉዳይ ቢሮ፣

፲፫ የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ፣

፲. **<u>የቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ተጠያቂነት</u>**

፩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ሥር የተዘረዘሩት የመስተዳድር ም/ቤት(ካቢኔ) አባላት በክልል

መስተዳድር ምክር ቤት(ካቢኔ) ለሚያሳልፋት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የሠፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ መ/ቤት የተቋቋመበትን ዓላማ መሠረት በማድረግ በዚህ አዋጅ ተለይተው የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት የመወጣት ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፩. <u>የቢሮና ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠሪነትና ተጠያቂነት</u>

፩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ መሠረት የክልል መስተዳድር ም/ቤት (ካቢኔ) አባላት የሆኑ የቢሮና ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሲሆን የሌሎች የቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ከተመለከቱት ውጪ ያሉ ጽህፈት ቤቶች፣ የልማት ተቋማት፣ ድርጅቶችና የሌሎች አስፈጻሚ አካላት ኃላፊዎች ተጠሪነት እንደ አግባብነቱ ለሚመለከተው የቢሮ ኃላፊ ወይም ለርዕሰ-መስተዳድሩ ይሆናል፡፡

## ፲፪. <u>የአስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

፩ የሥራ አመራር ማሰልጠኛ ተቋም ተጠሪነት ለአቅም ግንባታና ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ይሆናል፡፡

፪ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ እና የህዝብ አሰፋፈር፣ የምግብ ዋስትናና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ጽ/ቤት ተጠሪነት ለግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

፫ የፖሊስ ኮሚሽን፣የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት እና የሚሊሻ ጽ/ቤት ተጠሪነት ለአስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል፣

፬ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠርያ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ተጠሪነት ለጤና ጥበቃ ቢሮ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>የቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ስልጣንና ተግባራት</u>

## ፲፫. <u>የአቅም ግንባታና ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ</u>

፩ በፌዴራል የሚወጡ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ፈጻሚ ባለቤት እንዲኖራቸው በማድረግ አቀናጅቶ በበላይነት ይመራል፣

ለተግባራዊነታቸው የሚያስፈልጉ የህግ ማዕቀፎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣

፪ በክልሉ የልማት መርሃ ግብር የሚካተቱ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ይከታተለል፣ በበላይነት ያስፈጽማል፣ ውጤታማነታቸውንና ውስንነታቸውን ይገመግማል፣ የሚሻሻሉበትንም አማራጭ ያቀርባል፣

፫ በክልሉ መንግስት የሚነደፉ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የልማት እቅዶችን መነሻ በማድረግ አጠቃላይ የክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች የሚጠይቁትን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐት፣ የአሠራር ሥርዓትና ሌሎች የአቅም ግንባታ ፍላጐቶች ላይ ጥናት በማድረግ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ፖሊሲ ነክና ስትራቴጂያዊ እርምጃዎችን የሚመለከት ሀሳብ ያመነጫል፣

፬ በፌዴራል ደረጃ ተቀርጸው በሥራ ላይ የሚውሉ የተለያዩ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የሥልጠና ፕሮግራሞች በክልሉ በተገቢው አኳኋን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

፭ በክልሉ የተዋቀሩ አስፈጻሚ አካላት አንድ ወጥ የሆነ፣ ተደጋጋፊና የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት፣ የመረጃ አያያዝ፣ ልውውጥና አጠቃቀም፣ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት እንዲኖር ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

፮ የአቅም ግንባታ ሥራን ለማፋጠን የሚያስችሉ ተቋማት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ያጠናል፣ በአቅም ግንባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማትን ይገመግማል፣ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉበትን ስልት ይቀይሳል፣ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ፕሮግራሞች እንዲነደፉ ያደርጋል፡፡

፯ የግልና የሕዝብ ተቋማትን፣የማህበራትንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ያስተባብራል፡

፰ ተጠሪነታቸዉ ለቢሮዉ የሆኑ መ/ቤቶች የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የተሻሻሉ የአሠራር ሥርዓቶች እንዲሁም ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት አስፈላጊውን እገዛ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ በበላይነት ይመራል፡፡

፱ የመንግስት መ/ቤቶችን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም የሚያድግበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ለዚህም ተገቢውን እገዛ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

፲ ሥራ ላይ የዋሉ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ለመተግበር ከፌዴራል መንግስት መሰል ተቋማትና ከሌሎች ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፣በጋራ በመገናኘትም ፕሮግራሞቹ የበለጠ የሚዳበሩበትን፣ የሚሻሻሉበትንና

በክልሉ የሚኖረውን ግንዛቤ የሚዳብርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፲፩. በክልሉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐት መሠረት የተለያዩ የሀገር ውስጥ እና ውጭ ሀገር የትምህርትና ሥልጠና እድሎች በአግባቡ እንዲካሄዱ ያደርጋል፡፡

፲፪. የክልሉን መንግስት እና የአጠቃላይ ሕብረተሰብ የመፈጸም አቅም የበለጠ ለማሳደግ የሚችሉ የፖሊሲ ሀሳቦችን ያመነጫል፣ እንዲሁም የተለያዩ የሰው ኃይል ልማት ፕሮግራሞችን በመንደፍ በክልሉ ውስጥ ባሉ ተቋማት ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራነቱን ይከታተላል፡፡

፲፫. የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ በክልሉ ያስፋፋል፣ በልማት ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል፡፡

፲፬. በክልሉ ለዲሞክራሲ ሥርዓትና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ እገዛ የሚያደርጉ ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ለተግባራዊነታቸዉ ያስተባብራል፡፡

፲፭. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች አስተዳደርን በሚመለከት የወጡ ፖሊሲዎችና ህጐች በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣

፲፮. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በሚያወጣቸዉ የሥራ መደቦች የአመዳደብ መመሪያ መሰረት በክልሉ የመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ በሚገኙ የሥራ መደቦች ላይ ምደባ ይሰጣል፣

፲፯. ለመንግስት ሠራተኞች የተፈቀደውን የደመወዝ እስኬል፣የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን በሚመለከት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

፲፰. በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አቀጣጠር፣ አመዳደብ፣ ደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ ዝውውር እና የዲሲፕሊን ጉዳዮች በህጉ መሠረት መፈጸማቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ያረጋግጣል፡፡

፲፱. የክልል መስተዳድሩን የመንግስት ሠራተኞች ዝርዝር ሁኔታ መዝግቦ ይይዛል፣ስታትስቲካዊ መረጃዎች ያጠናቅራል፣ ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ያስተላልፋል፣

፳. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ አገልግሎታቸው እንዲራዘም ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

፳፩. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ለማሰናበት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

፳፪. ከክልሉ መንግስት ሠራተኞች ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በሚቀርቡ የይግባኝ አቤቱታዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

፳፫. ለክልሉ መንግስት ሠራተኞች የሥራ ውጤቶች መመዘኛ መመሪያ

ያወጣል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

፳፬. በክልሉ መንግስት መ/ቤቶች የሚደረጉ የጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥርን በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፣

፳፭. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች የፌዴራል ህጐችን በመተርጐም ረገድ ያጋጠሙ ችግሮችን ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ያስተላልፋል፣ በትክክለኛ ትርጓሜያቸዉ መሠረት መተግበራቸዉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

፳፮. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልል መንግስቱን አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም በመገምገም የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፣ሲፈቀድም ሥራና ሠራተኛ መገናኘቱን ያረጋግጣል፡፡

፳፯. በመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች፣ ልዩ ልዩ ጥናቶች፣ የማስፈጸሚያ ሕጐች፣ በተቀናጀ መንገድ የሚተገበሩበትን ስልት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

፳፰. የክልሉ መ/ቤቶች በስትራቴጂያዊ አመራር ዘይቤ የሚመሩበትንና የተቀናጀ የማሻሻያ ፕሮግራም አፈጻጸም ስልት የሚዳብርበትን ሥርዓት በመቀየስ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፣

፳፱. በክልሉ የሚገኙ አስፈጻሚ መንግስት መ/ቤቶች በለዉጥ ፕሮግራሞች ዙርያ ተገቢ የቴክኒክና የምክር አገልግሎት ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፴. የለዉጥ ፕሮግራሞች፣ ጥናቶችና ውጤቶችን አፈጻጸም በወቅቱ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያቀርባል፣ እንዲሁም በክልሉ አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ የማሻሻያ ጥናቶችን በመለየት የጥናት አፈጻጸም ቅደም ተከተል ያወጣል፣ መረጃዉንም በሥርዓት አደራጅቶ ይይዛል፣

፴፩. በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ረገድ የአገር ውስጥና የውጭ ተሞክሮዎችን በማጥናት ጠቃሚ ልምዶች ከክልሉ ሁኔታ ጋር ተገናዝበው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

## ፲፬. የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ

የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩ የሀገሪቱን የገጠር ልማት ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ስልቶች በክልሉ ውስጥ ያስፈጽማል፣ ይህንኑ መሠረት አድርጐ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘቡ የፖሊሲ ሃሳቦችን

ያመነጫል ሲፈቀድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

፪ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮችን ለተጠቃሚዉ ህዝብ ለማስረጽ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ምርታማነት እንዲያድግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

፫ የዱር እንስሳት ጥበቃና አጠቃቀም ደንቦችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፬ አግባብ ካላቸዉ አካላት ጋር በመተባባር ለግብርናና ገጠር ልማት መፋጠን አስፈላጊ የሆኑ የእርሻ መሣርያዎች፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች፣ የእንስሳት መድሃኒት፣ የብድር አገልግሎት እና ሌሎች የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች ወቅቱን ጠብቆ ወደ አርሶ አደሩ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፭ የግብርና ምርት የግብይት ሥርዓት፣ የህግ ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፮ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከምርምርና ከማሰልጠኛ ማዕከላት ጋር ተቀናጅቶና ተሳስሮ ይሰራል፣ ድጋፍም ይሰጣል፡፡

፯ የግብርና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ በግብርና እንቨስትመንት ዘርፍ ለተሠማሩ ባለሀብቶች ሙያዊ እገዛና ክትትል ይሰጣል፤ የግብርና ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፰ ተዛማች የሰብልና የእንስሳት በሽታ እንዲሁም ነባር የፀረ- ሰብል ተባይ ወረርሽኝ ሲነሳ አስቸኳይ የመከላከል ዕቅድ በማውጣት በክልሉ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞችን እንዲሁም የኀብረተሰቡን አቅም በማስተባበር በባህላዊና ዘመናዊ መንገድ አደጋውን ይከላከላል፡፡

፱ የክልሉ የደን ሀብት ልማትና የደን ጥምር እርሻ እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ ተስማሚ የሆኑ የደን ዛፍ ችግኞችን እንዲዘጋጁ የቴክኒክ አገልግሎት እንዲዳረስ ጥረት ያደርጋል፣

፲. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተፈጥሮ ሀብት መመናመን በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቆጣጠር የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ ስልትን እየቀየሰ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፲፩. በክልሉ ውስጥ በጥቅም ላይ የሚውሉ የእንስሳት መድኃኒት፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ይመዘግባል፣ በተገቢው መንገድም ስለመያዛቸው ይቆጣጠራል፡፡

፲፪. በክልሉ ውስጥ ጥራቱን የጠበቀ የእንስሳትና የአሳ ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል ድጋፍ ይሰጣል፣ ያበረታታል፡፡

፲፫. የሠብል፣ የእንስሳትና የእስሳት ተዋጽኦ ምርትና ምርታማነት እንድያድግ

ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ ምቹ ሁኔታን ያመቻቻል፡፡

፲፫. ቢሮው በሥሩ ለሚገኙ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት፣ ዕፅዋት ክሊኒክ፣ የገጠር ቴክኖሎጂ ማዕከል፣ አፈር ምርምርና እንስሳት ላብራቶሪዎችንና ማዕከላትን ለግብርናው ዘርፍ አገልግሎት ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፬. የክልሉ የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ እንዲጠበቅ የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ስልት ቀይሶ ይሰራል፡፡

፲፭. የነባር ብሔረሰብ ግብርና ዘይቤ በማጥናት የተፈጥሮ ሀብቱን አጠባበቅና ምርታማነትን ባገናዘበ መልኩ የግብርና ዘዴ ስልት በመቀየስ ብሔረሰቦች ከዘመናዊው የግብርና ቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቁ የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

፲፮. አነስተኛ የመስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

፲፯. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ ፪ ሥር የተመለከቱትን አስፈፃሚ አካላትና የልማት ተቋማት በበላይነት ይመራል፣ያስተባብራል፣ በተዋረድ ለዞንና ለወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት መ/ቤቶች ሙያዊ ድጋፍና እገዛ ይሰጣል፡፡

፲፰. አደገኛና መጤ አረሞች፣ በሽታዎችና ተባዮች ወደ ክልሉ እንዳይገቡ ተገቢዉን የመከላከያ ስልት ይነድፋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ በክልሉ ዉስጥ የሚገኙትንም እንዲወገዱ ጥረት ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸዉ ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ ያስተባብራል፣

፲፱. የግብርናና ገጠር ልማትን ለማስፋፋት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፲፭. <u>የንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርት እና ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ</u>**

የንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርት እና ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩ በንግድ፣ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ተቀናጅተው ውጤታማ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣

፪ በዘርፉ ከፌዴራል መንግስት እና ከክልል መንግስታት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን በበላይነት ያስተባብራል፣

፫ የሀገሪቱን የንግድ፣ ትራንስፖርትና ኢንዱስትሪ ፖሊሲን መሠረት በማድረግ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ተገናዝቦ አገልግሎት በብቃት እንዲሰጥና እንዲስፋፋ ያደርጋል፣ የቴክኒክና የምክር እንዲሁም የንግድ

ትራንስፖርትና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ በክልሉ የሚወጡ ተያያዥ ህጎች መከበራቸውን እና መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣

፬ በኢንቨስትመንት ፖሊሲና ህግ መሠረት የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሀሳቦችን በጥናት ያመነጫል፣ እንዲጠኑና በሥራ ላይ እንዲውሉ ያመቻቻል፣

፭ ሌሎች አግባብ ላላቸው አካላት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ የትራንስፖርት መገናኛ አውታሮች እንዲሰሩ፣እንዲሻሻሉና እንዲጠገኑ ሀሳብ ያቀርባል፣

፮ በክልሉ ውስጥ በንግድና ኢንዱስትሪ ሥራ ለሚሰማሩ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ፍቃድ ይሰጣል፣ያድሣል፣ይሰርዛል፣እንዲሁም ተገቢውን የአገልግሎት ገቢ ያሰባስባል፣ይቆጣጠራል፣

፯ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ እንዲያድግ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር አብሮ ይሠራል፣በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት የምክርና የሙያ አገልግሎት ይሰጣል፣ የፋይናንስ፣የገበያ የመሥሪያ፣የመሸጫ ቦታ ችግሮችን ለመቅረፍ ከሌሎች ጋር ይሠራል ያስተባብራል፣ እንደአስፈላጊነቱ የሙያ ማሻሻያ ማሰልጠኛ ማዕከሎች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ ማዕከላቱንም ያስተዳድራል፣

፰ በዕደ-ጥበባትና በሌሎች ኢንዱስትሪዎች የተሰማሩ አካላት ያመረቷቸውን ምርቶች የማሳያ ማዕከል እንዲያቋቁሙ ያግዛል፣ ያስተባብራል፣

፲. በክልሉ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ይመዘግባል፣ የቴክኔክ ምርመራ ያደርጋል፣ መንጃ ፈቃድ ይሰጣል፣ያድሣል፣ ይሠርዛል የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መናኸሪያዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡

፲፩. በክልሉ ውስጥ የመሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎት ሥርጭት አግባብ ባለው አካል የተወሰነ ዋጋ ተመን መከበሩን ይቆጣጠራል፣

፲፪. በክልሉ ውስጥ ለሚቋቋሙ መካከለኛና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የተሸከርካሪ መጠገኛ፣ ማደሻ ጋራዥ፣ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን መንዳት ለሚያስተምሩ ሰዎችና ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፫. በክልሉ ውስጥ የንግድ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል፤ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

፲፬. በክልሉ የንግድ ትርእትና ባዛር ወይም ኤግዚቢሽን ለማካሄድ ፍድና ድጋፍ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፭. በጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራ ዘርፍ የሚሠማሩ ግለሰቦችና ማህበራትን የደራጃል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፮. በክልሉ የንግድ መዝገብ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣

፲፯. በህዝባ ማመላለሻ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ግለሰቦችና ማህበራት ፍቃድ ይሠጣል፣ የተወሰነላቸዉን ደረጃ መጠበቃቸዉን ይቆጣጠራል፣ የስምሪት ፕሮግራማቸዉን ያጸድቃል፣ ተግባራዊነቱንም ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፰. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማረጋገጥ የሚመለከቱ ተግባራትን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፱. አማራጭ የትራንስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ መለስተኛ ጥናት ያካሂዳል፣ ያስፋፋል፣ ይተገብራል፣

፳. በክልሉ መንግስት በጀት ለሚሠሩ የመንግስት ግንባታዎች ዲዛይኖችንና የኮንስትራክሽን የሥራ ውሎች ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ግንባታዎች የሀገሪቱን ዲዛይን ኮድ መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣ መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት በክልሉ ለሚካሄዱ ግንባታዎች ሙያዊ እገዛ ያደርጋል፣

፳፩. በኮንስትራክሽን ዘርፍ መሠማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች የኮንስትራክሽን የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል እንቅስቃሴያቸውን ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፣

፳፪. ለከተሞች ህጋዊ ሰውነት ለመስጠተ እና ለውስጥ አሠራር የሚያስፈልጉ የህግ ረቂቆችን አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣የከተማ ልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

፳፫. ለከተሞች የእድገትና የድርጊት ፕላን ዝግጅት የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ አዲስ ፕላን ለሚያስፈልጋቸዉ ከተሞች ፕላን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ተዘ ጋጅቶ ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፣ የፕላን ግዜያቸዉን ለጨረሱ ከተሞች የፕላን ክለሳ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣

፳፬. ለከተሞች መሬት አስተዳደር የሚያስፈላጉ የህግ ማዕቀፎችን የዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸዉንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፳፭. በክልሉ የሚገኙ የከተማ አስተዳደሮች፣ ማዘጋጃ ቤቶችና ታዳጊ ከተሞች የበጀትና የዕቅድ አዘገጃጀትና አፈጻጸም፣ የሰው ኃይል ስምሪትና አስተዳደር፣ የገቢ አሰባሰብና የፋይናንስ አጠቀቀምን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፣

፳፮. የከተሞችን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ጥናት በማድረግ እና ለከተሞች ደረጃ አሰጣጥ መስፈረቶችን በመጠቀም፡-

ሀ/ በክልሉ ለሚገኙ ከተሞች ደረጃ ይሰጣል በከተማት ያልተመዘገቡና የከተማት መስፈርት የሚያሟሉትን በከተማነት መዝግቦ በመያዝ ለእድገታቸው ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል፣

ለ/ ማዘጋጃ ቤት ለማቋቋም በቂ አቅም ላላቸው መቋቋሚያ አዋጅ እንዲወጣ ያደርጋል፣እስኪወጣላቸው ጊዜያዊ ማዘጋጃ ቤት ጊዜያዊ የከተማ አስተዳደር እንዲቋቋምላቸው ያደርጋል፡፡

ሐ/ ማዘጋጃ ቤት ለማቋቋም በቂ አቅም ለሌላቸው ከተማች ማዘጋጃ ቤት ለማቋቋም በቂ አቅም እስኪፈጥሩ ድረስ በጥቂት የሰው ኃይል ጊዜያዊ ማዘጋጃ ቤት ወይም የከተማ አስተዳደር እንዲቋቋምላቸው ያደርጋል፣

፳፯. የከተማ ነዋሪዎችን የመጠለያ ችግር ለመቅረፍ የሚያስችሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተገንብቶ ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፉ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣

፳፰. በከተሞች ለንግድና ኢንቨስትመንት የሚዉሉ የከተማ ቦታዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

፳፱. የቢሮውን የሥራ ዕቅድ፣የበጀት ፍላጐት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተፈጻሚ ያደርጋል፣ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እያዘጋጀ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣

## ፲፯. <u>የአስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ</u>

የአስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩ በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩንና የኅብረተሰቡ ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

፪ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሕግ አስከባሪ አካላት ዲሞክራሲያዊ አመለካከታቸው እንዲዳብርና በሕገ-መንግስትና በሰብአዊ መብቶች ረገድ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ይሠራል፣

፫ በዞን፣ በልዩ ወረዳዎች ወይም በወረዳዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በሠላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፬ ከአጐራባች ክልሎች ጋር በሚያዋስኑ አካባቢዎች የሚነሱ አለመግባባቶች በሠላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣

፭ በአስተዳደር፣ በሕዝብ ደህንነትና በፀጥታ ሥራ ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው የፌዴራል መንግስትና ሌሎች ክልሎች አካላት ጋር ግንኙቶችን ያደርጋል፣

፮ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ጥያቄ ሲቀርብ በሕግ አግባብ መሆኑን ያረጋግጣል፣ይፈቅዳል፣ እንዲሁም ከተፈቀደለት ዓላማ ውጪ እንዳይሆን እና በሰላማዊ መንገድ መፈጸሙን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

፯ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ ፬ /፩-፫/ ሥር የተመለከቱትን አስፈጻሚ አካላት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል ::

፲፰. **<u>የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት</u>**

የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩. የሀገርቱን የቱርዝም ልማት ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የቱርዝም አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

፪. በክልሉ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የሚስፋፉበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤ በግል ባለሃብቶች ለሚቋቋሙ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋሞች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ተቋማቱ የተወሰነላቸውን ደረጃ መጠበቃቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የምክር አገለግሎቶችን ይሰጣል፣

፫. አግባብ ካላቸው የክልሉ መስተዳድር አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን የቱሪስት መስህቦችን ይመዘግባል፣ እንዲደራጁ፣እንዲስፋፉ፣ እንዲለሙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣

፬. ስለ ክለሉ የቱርዝም መስህቦችና የቱርዝም ልማት መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀናጃል፣ ያሠራጫል፣

፭. ቱርዝም ነክ በሆኑ ጉዳዩች አግባብ ያላቸው የክልል መስተዳድሩን አካላት ያስተባብራል፣

፮. በክልሉ የሚገኙ ቅርሶችን በሚመለከት የፖሊሲ ሀሳቦችን

ያመነጫል፣ኘሮጀክቶችን ይቀርፃል ይተገበራል ይከታተላል፣ ቅርሶች እንዲጠበቁና እንዲለሙ ያደርጋል

፯. የክልሉን ነባር ብሔረሰቦች ባህልና ታርክ በተመለከተ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል፣ ያስተዋዉቃል፣ የሚዳብሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፰. በክልሉ የባህል፣ የኪነ-ጥበብና የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

፱. በክልሉ የሚገኙ ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ ቅርሶች እንዲተዋወቁና እንዲጠበቁ እንዲታደሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

፲. ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተለይተዉ እንዲታወቁ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የሚወገዱበትን መንገድ ያመቻቻል፣

፲፩. በክልሉ የፎቶግራፍና የስዕል ኤግዝቢሽኖች በማዘጋጀት የክልሉን ተፈጥሮአዊና ባህላዊን ቅርሶች እንዲታወቁ ያደርጋል፣

፲፪. በዘርፉ የሚወጡ የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ህጐች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፫. በክልሉ ሙዚዬሞችና የህዝብ ቤተ-መጽሐፍቶች እንዲደራጁና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

፲፬. የቱርዝም ክፍለ ኢኮኖሚ ሥራዎች በፌዴራሉና በክልሉ መንግሥት ፖሊሲዎች መሠረት መመራቱን ይቆጣጠራል፣

፲፭. የቱሪዝም መስህቦችና ከቱሪዝም ጋር የተያያዙ ሥራ ውጤቶች እንዲታወቁ ኤግዚቢሽን ያዘጋጃል፣ በሌሎች ክልሎች በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ላይም ይሳተፋል፣

፲፮. የቱሪዝምን ልማት የሚመለከቱ ጥናቶችን ያካሄዳል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ያጠናክራል፣ ለሚመለከተው ክፍል ያስተላልፋል፣

፲፯. የቱሪዝም ልማት ሥራ ለማካሄድ ለሚፈለጉ የሀገር ውስጥ ባለ ሀብቶት የምክር አገልግሎትና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሥራቸዉን ይቆጣጠራል፣ ያበረታታል፣

፲፰. የቱሪስት አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ይቆጣጠራል፣ ደረጃቸው እንዲሻሻል የምክር አገልግሎትም ይሰጣል፣

፲፱. የቱሪስት መስህብነታቸው ለቱሪዝም ልማት ብቻ መዋል

የሚገባቸውን ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣ የልማት ሁኔታቸውንም ይቆጣጠራል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

፳. የቱሪስት መዳረሻ በሆኑ ሥፍራዎች የሚኖረው ህብረተሰብ ከቱሪዝም ልማት ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል፣ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያውላል፣

፳፩. በቱሪዝም ዋና ዋና መስህቦች አካባቢ የመሠረተ ልማት እንዲስፋፋ ጥናት ያደርጋል፣ ለሚመለከተው ክፍል ያስተላልፋል፣ ውሳኔ ሲያገኝ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

፳፪. የክልሉ የቱሪዝም ሀብቶች እንዲጠበቁና እንዲታወቁ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም የማስተዋወቅ ሥራ ያከናውናል፣ የአገር ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲያበረታታ ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

፳፫. የክልሉ የተለየ የቱሪዝም ፖቴንሺያል የሆነውን የኤኮ-ቱሪዝም መዳረሻ ልማት ላይ ያተኮረ ሥራ ይሰራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆንም መስህቦቹ እንዲጠበቁ የግንዛቤ ማሻሻያ ሥራዎች ያከናውናል፣

፳፬. የሆቴሎችና የቱሪዝም ሥራ ማሠልጠኛ ተቋሞች በክልሉ የሚስፋፋበትን ስልት ይቀይሣል፣ ሥራቸውን ይቆጣጠራል፣ ይመራል፣

፳፭. የመታሰቢያና የስጦታ ዕቃዎች ምርትና አቅርቦት ሊሻሻል ስለሚችልበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሠራል፣የምክርና የቴክኒክ ዕገዛ ይሠራል፣

፳፮. የጽ/ቤቱን አላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣

## ፲፱. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩. የሀገሪቱ የልማት ዕቅድና ስትራቴጂ ላይ የተመሰረተና በክልል መንግስት የሚፈጸም የረዥም፣የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት እቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

፪. ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግስት አካላት ጋር በመተባበር በረዥም

በመካከለኛና በአጭር ጊዜ ዕቅዶች ውስጥ የሚንፀባረቁ በክልሉ መንግስት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑና እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡

፫. የየሴክተሩን እቅድ አፈጻጸም እየተከታተለና እየገመገመ የተቀነባበረ ሪፖርት በየሶስት ወሩ ለክልሉ መንግስት ካቢኔ ያቀርባል፣

፬. የክልሉ መንግስት አካላት የሀገሪቱን የፋይናንስ ፖሊሲዎችን፣ህጎችን፣ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከትለው መስራታቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

፭. የክልሉ መንግስት ከሀገር ውስጥ ባንኮች የሚያገኘውን ብድር በክልሉ መንግስት ስም ተደራድሮ ይፈርማል፣ ብድሮችን እየተቆጣጠረ ያስተዳድራል፡፡

፮. የክልል መንግስቱን የፋይናንስ ክንውን ይዞታና አስተዳደር የሚያስረዳ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ ለክልሉ መስተዳድር ካቢኔ ያቀርባል፡፡ ለአመቱ ከተዘጋጀው በጀት ሌላ ተጨማሪ በጀት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በተገቢው አካል ሲፈቀድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡

፯. ስለ ክልሉ የፋይናንስ አያያዝና አጠቃቀም ጥናት እያደረገ የመፍትሄ ሃሳብ ያመነጫል

፰. በሌላ የክልሉ መንግስት አካል የማይተዳደር ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ የክልሉ የመንግስት ሀብትና ንብረት ኃላፊ ሆኖ ያስተዳድራል፡፡

፱. ከክልሉ የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶችና የመንግስት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡትን መደበኛና የካፒታል በጀት ትክክለኛነት እየመረመረ ዓመታዊ በጀት አጠቃሎ በማዘጋጀት ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ያስተዳድራል፡፡

፲. የክልሉ መንግስት መ/ቤቶች ግዥና ንብረት አስተዳደር መመሪያ ያወጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል፡፡

፲፩. የክልሉን የተፈጥሮ ሀብት፣ ሕዝብ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ስርጭትና የአገልግሎት መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፡፡

፲፪. ለክልሉ ልማትና እድገት የሚያስፈልጉ የቅየሳ፣ የካርታና የጂኦግራፊ ጥናት ሥራዎች እንዲከናወኑ ያደርጋል፡፡

፲፫. ስነ-ሕዝብን በሚመለከት የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጐች በክልሉ ውስጥ በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣ስለአፈጻጸማቸውም ስልቶችንና ስትራቴጂዎችን ይቀይሣል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንም ስነ-ሕዝብን ጉዳይ እንዲሳተፉ ያስተባብራል ፣ ጥናቶችንና ምርምሮችን ያደርጋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፬. የክልሉን ህዝብ ልማት በበላይነት ይመራል፣ያስተባብራል፣ይከታተላል፣ ይገመግማል ጥናቶችን ያካሂዳል ፡፡

፲፭. በክልሉ ውስጥ ለመሥራት ፍላጐት ላላቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና መንግስታዊ በጐ አድራጊ ድርጅቶች አስፈላጊውን ትብብር በማድረግና መረጃ በማቅረብ እንዲሁም የሚያቀርቡትን የልማት ዕቅድ በመመርመርና ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ ይዋዋላል፣ ያስተባብርል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይገመግማል፣ ከገቡት ውል ውጪ የሚንቀሳቀሱ ካሉ ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣

፲፮. ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር በክልሉ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎ እንዲበረታታ ድጋፍ ሰጭ የሆነ አመልካች እቅድ ያዘጋጃል፡፡

፲፯. በክልሉ እስከ ወረዳ ድረስ የሚካሄደውን የበጀት ድልደላ ቀመር ያዘጋጃል፣በሚመለከተው አካል ያጸድቃል፡፡

## ፳. የስፖርት ኮሚሽን

የስፖርት ኮሚሽን የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩ የአገሪቱን ስፖርት መሰረት በማድረግ የአካል ማሰልጠኛና ስፖርት በክልሉ ውስጥ ያስፋፋል::

፪ በክልሉ ውስጥ ለሚቋቋሙ የስፖርት ማህበሮች ፍቃድ ይሰጣል፣ ፐሮግራሞችን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፫ ክልል አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን ያዘጋጃል፣ ተወዳዳሪዎችና የስፖርት ልዑካን አባላት በእንክብካቤ እንዲያዙና

በሚገባ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

፬ ክልል አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን በሚመለከት በስፖርት ማህበሮች መካከል የሚነሳውን ክርክር ይዳኛል፣ እልባት የሚያገኙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣

፭ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቅና መሳሪያ ከአገር ውስጥ ወይም ከውጭ ሃገር የሚገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

፮. ስፖርት ህዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ያደርጋል፣የክልሉ ባህላዊ ስፖርቶች የበለጠ እንዲታውቁ፣እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያደርጋል፡፡

፯. የክልሉ የስፖርት ማህበር ገቢ ለታለመላቸዉ አላማ ብቻ መዋሉን ያረጋግጣል፣ ሂሳባቸውን ይመረምራል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፣

፰. በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚያገለግሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል ወይም አስተዳደራቸዉን ይከታተላል፣

፱. ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር ስፖርታዊ ህክምናን ያደራጃል፡፡

## ፳፩. <u>የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ</u>

የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

፩ ስለውሃ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመከተል የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ የማሲፈጸሚያ ህጎችን ያመነጫል፤ ለተግባረዊነታቸዉ ይሰራል፣ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣

፪ በክልሉ ውስጥ ሚገኙ ሸለቆዎችን፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን ክምችትና ስርጭቶችን ያጠናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይመዘግባል፤ ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በሚካሄዱ ጥናቶች ይሳተፋል፣ በስራ ላይ ዕንዲውሉ የደርጋል፣

፫ የክልሉ ውሃ ሀብት በልዩ ልዩ የግልጋሎት አይነቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መከፋፈሉንና ጥቅም ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፣

፬ የክልሉን የውሃ ሀብት በሚመለከት ማንኛውንም የውሃ ሥራዎች ለመስራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፍቃድ ይሰጠጣል፤ ከፍተኛ ደረጃ የውሃ ሥራ ፈቃዶችን በሚኒስቴር መስሪያ ቤት እንዲሰጡ ያመቻቻል፣ ይቆጣጠራል፣

፭ የክልሉን የውሃ ክፍያ ታሪፍ በተመለከተ ጥናቶች ያካሂዳል፣

ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ያቆጣጠራል፣

፮ ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች ለሚውል ውሃ የጥራት ደረጃ ይወስናል፤ በተወሰነውም የጥራት ደረጃ መሰረት ፍሳሾች የተወሰነውን የጤናማነት ደረጃ በክልሉ ውስጥ በሥራ ለይ መዋሉን የከታተላል ይቆጣጠራል፣

፯. ከማዕከል የሚኒስቴር መ/ቤት ጋር በመወያየት የውሃ ሀብት አጠቃቀምን ይወስናል፤ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛማድ በሥራ ይተገብራል፣

፰. በክልሉ በውሃ ሥራ ላይ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ይተባበራል፤የሥራ አፈጻጸማቸውን
ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፡

፱. የሜትሮሎጂና የኃይድሮ ጂኦሎጂ መረጃዎችን በመሰብሰብ ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፤ መረጃዎችን ለቀጣይ ጥናት ያደራጃል፡፡

፲. የውሃ ሀብት ልማት ጥናቶችን ያካሄዳል፣ዲዛይኖችን ይሠራል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል፣ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡

፲፩. ንፁህ የመጠጥ ውሃ በክልሉ ከተሞችና የገጠር ሕብረተሰብ የሚዳረስበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ አቅም በፈቀደ መጠን ለቤት እንስሳት የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ያመቻቻል፣

፲፪. የክልሉ ሕብረተሰብና ባለሀብቶች በውሃ ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታል፣ ተገቢውን የሙያና የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል፤ በክልል ደረጃ የሚሠሩ የውሃ ሥራዎች ፈቃድ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፲፫. የመጠጥ ውሃ ተቋሞችን የእንክብካቤ መጠን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ በውሃ ልገሳቸው አቅም ላይ ጥናት ያካሄዳል፣ በጥናቱ ውጤት ላይ የተመሰረተ መፍትሔ ይሰጣል፣

፲፬. በሴክተሩ ለሚሠሩ ተቋማትና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፣

፲፭. በሴክተሩ ለወረዳዎች፣ለዞኖችና በውሃ ሥራ ላይ ለተሠማሩ አካላት የቴክኒክ ድጋፍ
ያደርጋል፣ይከታተለል፣ይቆጣጠራል፣

፲፮. ለማዕድንና ኢነርጂ ጥበቃና አጠቃቀም የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመከተል የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ ሕጎችን ያመነጫል፣ ያወጣል፤ የወጡትንም በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣

፲፯. የማዕድን ሀብትን በመጠበቅ ረገድ ከማዕድንና ኢነርጂ ሚንስቴር ጋር በመተባበር ይሠራል፤ በክልሉ ውስጥ ለሚካሄደው የማዕድንና ኢነርጂ ልማት ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ የልማት ፈቃድ ያወጣል፣

፲፰. በክልሉ የሚገኙ ለመስኖ ልማት ሊውሉ የሚችሉ ማንኛውም እምቅ የውሃ ሀብት ያጠናል፣ ለመስኖ ልማት እንዲውሉ ያደርጋል፣

፲፱. በክልሉ የሚገኙ ማንኛውንም የውሃ ሀብት ያስተዳድራል፣ ለልማት እንዲውሉ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣

፳. ውሃ ነክ ጉዳዮች የማማከር፣ የውሃ ሥራ ፈቃድና ሙያዊ ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ይሠጣል፣

፳፩. በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የውሃ ሥራዎች የቁፋሮ ደረጃዎች ያወጣል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ሥራውም ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የወጡ ሕጎችን የተከተለ ስለመሆኑ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣

፳፪. በክልሉ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ለማዳረስ በነዳጅ ኃይል የሚሠሩ አነስተኛ የውሃ ኃይል ማምንጫ ጣቢያዎች ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ያጠናል፣ ስፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይልና ታዳሽ ኃይሎች የማመንጨትና የማሰራጨት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣

፳፫. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የሚያስፈልገውን ጋዝ፣ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች የሚያቀርቡበት ሁኔታ ያመቻቻል፣ የተወሰነ ኢነርጂ መጠባበቂያ ክምችት እንዲኖር መደረጉን ያረጋግጣል፣

፳፬. ባህላዊ ማዕድን ማምረቻ ሥራዎችን ያበረታታል፣ የኮንስትራክሽን ማዕድን፣ የከበሩ ማዕድናት የፍለጋ፣ የምርመራ፣ የማምረት ሥራና የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ፈቃድ ይሰጣል ይቆጣጠራል፡፡

## ፳፪. <u>የጤና ጥበቃ ቢሮ</u>

የጤና ጥበቃ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩ የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሰረት በማድረግ የክልሉ ህዝብ ጤና የሚጠበቅበትን ዕቅድና ፕሮግራም፣ ያዘጋጃል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፡

፪ ስለህዝቡ ጤና አጠባበቅ የሚወጡ ህጐች ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ደንቦችና መመያዎች ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣

፫ በክልሉ ውስጥ በሚቋቋሙ ሆስፒታሎች፣ጤና ጣቢያዎችና ጤና ኬላዎች የምርምር የማሰልጠኛ ተቋሞችን ያደራጃል ያስተዳድራል፣

፬ በሀገር ውስጥ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ለማቋቋም የጤና ጣቢያዎች፣የክሊኒኮች የላቦራቶሪዎችና የፋርማሲዎች ፈቃድ ይሰጣል በሀገር አቀፍ ደረጃ

የወጣውን ደረጃ ጠብቀው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፣

፭ በክልሉ ውስጥ በህዝብ ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፣

፮ ፍቱንነታቸውን የተረጋገጠ የባህል መድኃኒቶችን የህክምና ዘዴዎች ከዘመናዊ ህክምና ጋር ተዋህደው ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣የምዝገባ ደንብና ስርዓት እንዲኖራቸው ያደርጋል፣

፯ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት ክትባቶች እንዲሰጡና ሌሎች ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፣

፰ የህዝቡን ጤና ለመጠበቅ በሚደረግ የኳራንቲን ቁጥጥር ይሳተፋል፣ በጠረፍ አካባቢ እንዲቋቋሙ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣

፱ የምግቦችንና መጠጦችን ለጤና ተስማሚነት ያረጋግጣል፣ የአገልግሎት ሰጭ ተቋሞችን የንፅህና አያያዝ ይቆጣጠራል፣

፲. የጤና ፖሊሲውን መሰረት አድርጐ ህዝቡ በበሽታ መከላከል ላይ በስፋት የሚሳተፉበትን፣ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣

፲፩. ስለሥራው አፈጻጸም ወቅታዊ መረጃዎችን እያዘጋጀ ለክልሉ መስተዳድርና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴርያቀርባል፣

፲፪. በክልል ውስጥ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

፲፫. በጤና ዘርፍ በሁሉም ደረጃዎች ለሚገኙ የጤና ሠራተኞች አስተዳዳሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሀይሎች ከጤና አገልግሎቱ ዓላማዎች አቅጣጫ ተገቢና ተከታታይ ሥልጠና ይሰጣል፣

፲፬. በጤና አገልግሎት ሥርዓት በሁሉም ደረጃዎች የሚያስፈልጉና ደረጃቸውን የጠበቁ መድኃኒቶችና መሣሪያዎች አቅርቦት በየጊዜው ያሻሽላል፣

፲፭. መድሃኒቶችን፣ የክትባት መገልገያዎችን፣ የክሕምና ቁሳቁሶችን፣ መማሪያዎችን በየአይነታቸውና እንደ አስፈላጊነታቸው ለጤና ተቋማት አቅርቦት ያሳድጋል፡፡ የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች መለዋወጫ አቅርቦት ጥገናና እንክብካቤ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

፲፮. በዋና ዋና የጤና ችግሮችና የጤና አገልግሎት ሥርዓቶች ተግባራዊ ምርምር ያስፋፋል፣

፲፯. የተለመዱ የሕፃናት በሽታዎችን በተለይ የተቅማጥ የመተንፈሻ አካላት ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ባሉት የጤና

መገልገያዎች በወቅቱ መጠቀምና የወጣቶች ልዩ የጤና ችግሮች ከዕድሜያቸው ጋር የተያያዙ የጤና ፍላጐቶች ላይ ትኩረት ማድረግ፣

፲፰. አግባብ ያለው የሥራ ፈቃድ በመስጠት የግል የሕክምና ድርጅቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

፲፱. በክልል መስተዳድር ም/ቤትና በርዕሰ መስተዳድሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፳፫. <u>ፍትህ ቢሮ</u>

የፍትህ ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

፩ የሕግ ጉዳዮችን በሚመለከት የክልሉ መንግስት አማካሪ ሆኖ ይሰራል፣

፪ በሌሎች ህጎች ለሌሎች አካላት የተሠጠ የወንጀል ሥልጣን እነደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ወንጀሎች የክልሉን መንግስት በመወከል ይከራከራል፣

፫ የክልሉን ዐቃቤ ህግ በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

፬ ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ በሕጉ መሠረት አጥፊዎችን ተከታትሎ በመያዝ በአጥፊዎች ላይ የወንጀል ምርመራ ያካሂዳል፣በሕጉ መሠረት ለፍርድ ቀርበው ተገቢውን ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

፭ በማረሚያ ቤት፣በማረፊያ ቤት፣በፀባይ ማረሚያና ጊዜያዊ የእስረኞች መጠለያ የሚገኙ ሰዎች በአግባቡ መያዛቸውንና ህጋዊ መብታቸው መከበሩን ያረጋግጣል፣

፮ በክልሉ መንግስት ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል፣ በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ ያነሳል፣

፯ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የወንጀል መንስኤዎችን ያጠናል፣ለወንጀል መከላከል የሚረዱ ጥናቶች ያካሂዳል፣ወንጀል የሚቀንስበትን ስልት ይቀይሳል፣

፰ ለወንጀል ድርጊት ምስክሮች እንደአስፈላጊነቱ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

፱ በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው በክልሉ ፍ/ቤቶች ክስ ለመመስረትና ለመከራከር አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች ካሳ እንዲያገኙ በፍትሀብሔር ክስ ይረዳል፣

፲. የእያንዳንዱ መ/ቤት የመንግስትና የህዝብ መብትና ጥቅም የማስከበር

ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝቡን እንዲሁም የክልሉን መንግስት መብትና ጥቅም ለማስከበር በፌዴራልና በክልሉ ፍ/ቤቶች በማንኛውም ዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባዔ ክስ ይመሰረታል፣ክስ እንዲመሠረት ያደርጋል፣ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፣

፲፩. የክልሉ መንግስት ወይም አካላቱ ተከራካሪ የሚሆኑባቸውን የፍትሐብሄር የመብት ጥያቄዎችን አያያዝ እንደአስፈላጊነቱ ይከታተላል፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፣ ለዚህም ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደቡን ያረጋግጣል፣

፲፪. በክልሉ መንግስት ወይም በአካላቱ ጥያቄ ሲቀርብለት የህግና ደንቦች ረቂቅ በማዘጋጀት ይረዳል፣

፲፫. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በትርፍ ላይ ያልተመሠረተ ዓላማ ይዘው የተቋቋሙና በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ማህበራትን ይመዘግባል፣ፈቀድ ይሰጣል፣

፲፬. በክልሉ መንግስት ፍ/ቤቶች ለመከራከር ለሚችሉ ጠበቆች ፈቃዱ ይሰጣል፣ይቆጣጠራል፣

፲፭. ከሰብአዊ መብት አጠባበብ አንፃር የህዝብን ንቃተ-ህግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች የህግ ትምህርት ይሰጣል፣የህግ ትምህርት ስልጠናንና በሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፣

፲፮. የክልሉን ሕጐች የማጠቃለል ስራ ያካሂዳል፣

፲፯. በክልሉ ውስጥ የውልና ማስረጃ ምዝገባ አገልግሎት ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሲሆን እንዲደራጅ ያደርጋል፣

፲፰. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለክልሉ ዳኞች፣ዐቃብያን ሕግ፣ለፖሊስ ሌሎች አመራር አካላት እንደአስፈላጊነቱ የሥልጠና ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፣ ሥልጠናም ይሰጣል።

፲፱. ለባህላዊና ልማዳዊ የዳኝነት አካላት አስፈላጊውን ስልጠና ይሰጣል፣

፳. የክልሉ የፍትህ አስተዳደርና አገልግሎት ሥርዓት የሚሻሻልበትን መንገድ ያጠናል፣በአግባቡ ተደራጅቶ ለክልሉ ሕብረተሰብ ተገቢውን አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

## ፳፬. <u>የትምህርት ቢሮ</u>

የትምህርት ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩ በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ መሰረት የክልሉን የትምህርት

ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣

፪ በክልሉ ለትምህርት የደረሱ ሁሉ የመማር ዕድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል፣ መሠረታዊ ትምህርትን ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል፣

፫ የክልሉ የትምህርት ጥራት በአገር አቀፍ ደረጃ የተወሰነለትን ስታንደርድ የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፬ የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲና ስታንዳርድ ተከትሎና የክልሉንና የአካባቢውን ሁኔታዎች በማገናዘብ የክልሉን አንደኛ ደረጃ ስርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፣ እንዲሁም በትምህርት ሚኒስቴር የሚዘጋጀዉን የሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ሥራ ላይ ያዉላል፣

፭ በደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥኑም ያደርጋል፣

፮ የመጀመሪያ ትምህርትን በነባር ብሄረሰቦች አፍ መፍቻ ቋንቋ ለመስጠት ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፣

፯ በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው ለክልሉ ት/ቤቶች የሚሰጡ ፈተናዎችን ተከታትሎ ያስፈጽማል፣በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው የሚሰጡትን ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣ የምስክር ወረቀቶችን ብቃት ያረጋግጣል፣

፰ ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ የመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍትና ሌሎች ድጋፍ ሰጭ ማጣቀሻ መጽሐፍት እንዲሁም ሌሎች የትምህርት መሳሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣

፱ በክልሉ የሚገኙትን የትምህርት ተቋማትን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፣ይከታተላል፣ እገዛ ይሰጣል፣

፲. በክልሉ የትምህርት ተቋማትን ግንባታ ያካሂዳል፣ ያደራጃል፤ ደህንነታቸዉን ይከታተላል፣

፲፩. የክልሉን የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና ኮሌጆችን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣

፲፪. በድርጅቶችና ባለሀብቶች ለሚቋቋሙ እስከ ኮሌጅ ደረጃ ላሉ የትምህርት ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣የብቃት ደረጃ ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፣

፲፫. ለትምህርት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

፲፬. ለክልሉ ነባር ብሔረሰቦች፣ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ልዩ ፍልጎት ትምህርት ለሚሹና ለጐልማሶች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፭. የክልሉ ትምህርት ፕሮግራም በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ያደርጋል፣

፲፮. የትምህርቱን ሥራ ማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄዱ ጥናቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፯. የትምህርት መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፣

፲8. ለትምህርት ሥራ አስፈላጊ ድጋፍ ለማግኘት እንዲቻል ህብረተሰቡንና መያዶችን ሊያሳትፍ የሚችል ስልት ይቀይሳል፣ ያስተባብራል፣

፲፱. ከትምህርት ሥራ ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ ጉዳዮች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት አብሮ ይሠራል፣

## ፳፭. <u>የሴቶች፣ የወጣቶችና የህፃናት ጉዳዮች ቢሮ</u>

የሴቶች፣ የወጣቶችና የህፃናት ጉዳዮች ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. ሴቶችና ወጣቶች በክልሉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳታፊነታቸዉንና ተጠቃሚነታቸውን ሊያረጋግጡ የሚያስችሉ ዕድሎችን ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር ያመቻቻል ፣

፪. በክልል ደረጃ የሴቶች የወጣቶችና የህፃናትን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚረዱ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ ስልት በመቀየስ ለተግባራዊነቱም የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣ አስፈላጊውን ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፣

፫. የሴቶች፣ የወጣቶችና የህፃናትን ተሳትፎ ለማጎልበት እና በህብረተሰቡ ዘንድ ያለዉን የተዛባ አመለካከት ለመቀየር የሚረዱ የግንዛቤና የንቅናቄ መድረክ ያመቻቻል ፣

፩. በክልሉ መንግሥት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ሕጐች፣የልማት ፕሮግራሞች ፕሮጀክቶች ፓኬጆች የሴቶች፣ የወጣቶችንና የህፃናት ጉዳዮች እንዲካተቱ ስልት ይነድፋል ፣ይገመግማል፣ተገቢውን ክትትል ያደርጋል ::

፭. በሴቶች እና በህፃናት ላይ የሚፈጸሙ የሃይል ጥቃቶቸና መድሎዎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በጥናት በመለየት የሚወገዱባቸውን የመፍትሔ ሃሳቦች ያቀርባል የወጡትን ህጎች አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

፮. በሀገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ የወጡትን የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ በክልሉ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣

፯. ሴቶች ወይም ወጣቶች እንደ ፍላጐቶቻቸውና እንደ ችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ሁኔታዎችን ያመቻቻል

፰. ሴቶችን፣ ወጣቶችንና ሕፃናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች አገር አቀፍና ክልላዊ ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ የልማት ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ፓኬጆች በክልሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያስተባብራል፣ አፍጻጸማቸውን ይከታተላል ፣ይገመግማል፤ ክልላዊ ፖሊሲዎችንና ህጎችን፣ ያመነጫል

፱. የሴቶችን፣ የወጣቶችንና የህጻናትን ሁለተናዊ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያጠናል ወይም ያስጠናል፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ፈንድ ያፈላልጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፲. በክልል አቀፍ ደረጃ ጤናማና ኃላፊነት የሚሰማው የወጣት ኃይል ለማፍራት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ይቀይሣል፣ የሚተገበሩትን ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥራል፣

፲፩. የክልሉ ወጣት ሕገ-መንግስታዊ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ህደት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፪. በወጣት ጥፋተኝነትና ሥራ አጥነት ዙርያ ከሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል፣ አስፈላጊዉን ድጋፍ ያድርጋል፣

፲፫. የሕፃናት መብትና ደህንነት እንዲጠበቅ ይሰራል፣ የሚመለከታቸው አካላትን ያስተባብራል፣

፲፬. በክልሉ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ሴቶችን፣ ወጣቶችንና ህፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዩች ዙሪያ አብሮ ይሰራል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፣ይከታተላል፣አፈፃፀማቸዉን ይገመግማል፣

፲፭. ሴቶች በክልሉ ዉስጥ በሚሰጡ ስልጠናዎች፣ ደረጃ ዕድገት፣ ቅጥር የትምህርት ዕድል፣ እንዲሁም በተለያዩ ኮሚቴዎችና የውሳኔ ሰጪ ቦታዎች ዉስጥ በሚገባ መወከላቸዉን ይከታተላል፣ የተደራጀና የተጠናከረ መረጃ ይይዛል፡የማስተካከያ እረምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል

፲፮. በክልሉ የህግ አውጪ፣ በህግ አስፈጻሚውና ህግ ተርጓሚው የመንግስት አካላት አደረጃጀት ዉስጥ ወጣቶችና ሴቶች በውሳኔ ሰጪ ቦታዎች ላይ በሚገባ መወከላቸዉን ያረጋግጣል፣ይከታተላል፣

፲፯. በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ዉስጥ የሚገኙትን ሴቶች፣ ወጣቶችና ህጻናትን ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን የጠናል ወይም ያስጠናል፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ

ፈንድ ያፈላልጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

፲8. የእያንዳንዱ ሴክተር መስሪያ ቤት እቅድና ሪፖርት ሥርዓተ ጾታን ያገናዘበ መሆኑን ይገመግማል ወይም ያስገመግማል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡

፳፮. **<u>የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት</u>**

የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

፩ ለመንግሥት የኮሙኒኬሽን ሥራ አመራር መስጠትና በመስኩ መልካም አፈጻጸም የሚኖርበትን ሥርዓት መፍጠር ፣

2 ለክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አቅጣጫ ማስቀመጥና ማስተባበር ፣

3 የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሕዝብ ግንኙነት ሠራተኞችን የአቅም ግንባታ ተግባሮች ማከናወን፣አጠቃላይ የሥምሪትና የእድገት አቅጣጫ መወሰን ፣

4 የመንግሥት ቃል አቀባይነት ሥራን ጨምሮ የመንግሥት ኢንፎርሜሽን ዋነኛ ምንጭ በመሆን ማገልገል፣የመንግሥትን መልዕክቶች መቅረጽና በልዩ ልዩ መንገዶች ማሰራጨት፣በሀገራዊና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ የመንግሥትን አቋም መግለጽ ፣

5 የመንግሥት የኮሙኒኬሽን ፕሮግራሞችን ይዘትና አፈጻጸም ማቀናጀት ፣

6 የሀገር ውስጥና የውጭ የክልል ሚዲያ የዕለት ተዕለት ዘገባ ቅኝት ሥራዎችን በማከናወንና የሕዝብ አስተያየት በማሰባሰብ መተንተንና ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፣

7 በመንግሥት ፖሊሲዎችና በተለያዩ ሃገራዊ ጉዳዩች ላይ ግንዛቤ ለመስጠትና ግልጽነትን ለመፍጠር ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀትና ማስተባበር ፣

8 የክልሉ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ህብረተሰቡን በአካል አግኝተው እንዲያነጋግሩና ተቋማትን በመጐብኘት የሥራ ክንውኖችን እንዲገነዘቡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

9 በክልሉ መ/ቤቶችና በወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ኮሙዩኒኬተሮች ጋር ጠንካራ የግንኙነት ሥርዓት መፍጠር፣ እንዲሁም የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት፣

10 የክልሉ የመንግሥት የዌብሳይት ሥራዎች መሥራት፣

11 ልዩ ልዩ የሕትመትና ኦዲዮ ቪዲዮ ምርቶችን ማምረት፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የፎቶ ግራፍና የኦዲዮ ቪዲዮ ቀረፃና የአርማና የህትመት ዲዛይን እንዲሠራላቸው ሲጠይቁ የማዘጋጀትና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣

12 ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጋዜጠኞች በየወቅቱ መግላጫ ይሰጣል፣

13 ክልሉ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም ልታወቅበት የሚችልበትን ትክክለኛ ገጽታ ሰፊ መረጃ መስጠት፣በኢትዩጵያ ሆነ በክልሉ ላይ የሚነሱ የተሳሳቱ መረጃዎችን መመከት፣

14.በኮሙዩኒኬሽን ሥራ ዙሪያ በሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለ ድርሻ ወገኖች መካከል በጋራ ፍላጐት ላይ የተመሰረተ የአጋርነት ሥርዓት መዘርጋት፣

15.የሚዲያ መሠረት ልማት የሚያድግበትንና ብቃት ባለው ባለሙያ የታገዘና በክልል ብዙህነት ላይ የተመሠረተ ሚዲያ እንዲገነባ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ፣

16.በኢንፎርሜሽን፣ በኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ፣

17. ለሚሠጠው አገልግሎት እንዳስፈላጊነቱ በሕግ መሠረት ክፍያ መሰብሰብ፣

18. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

፲፱ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን ፣

## ፳፯. የአከባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ

የአከባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የሚከተሉ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል

፩. በፌደራል የአካባቢ ፖሊሲ ላይ ተመስርቶ የክልሉን የአካባቢ ህጎችና ስልቶች እንዲሁም የገጠር መሬት አስተዳደርናአጠቃቀም ፖሊሲና ህጎችን ጸ□□ጽል፣ ሲናትቅም በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸዉንም ይከታተላል::

፪. በክልሉ ውስጥ በሚካሄድ የልማት ፕሮጀክቶች፣ ፖሊሲዎችና ስልቶች ላይ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ስርዓት ይዘርጋል::

፫.የማህበራዊና ኢኮኖማያዊ ልማት ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ የሚኖራቸው ጉልህ ተፅዕኖ እንዲገመገም ከፕሮጀክቱ አቅራቢዎች የአካባቢ ተፅዕኖ ዘገባ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ዘገባዎችን በመመርመር የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣

፬. የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ዕቅዶችና መርሀ ግብሮች በስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ከአካባቢ ጥበቃ ቁጥጥርና ክትትል አንፃር ለዘላቂ ልማት ያላቸውን አስተዋጽኦ በመመልከት የውሳኔ ሀሳብ ለመንግስት ያቀርባል::

፭. በአካባቢ እንክብካቤ እና ልማት የተሰማሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የማህበረሰቦች ማህበራትን እና መንግስታዊ አካላትን ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ያስተባብራል::

፮. በህግ የተደነገጉ የፌደራሉ የአካባቢ ደረጃዎች ሳይጣሱ የክልሉን የአካባቢ ደረጃዎች ያዘጋጃል፣ ሲጸድቁም

አግባብነት ሳላቸው አካላት ያሳውቃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል::

፯. በረሃማነትን ለመከላከልና የተጎሳቆሉ ወ□ም □ተራቆቱ አካባቢዎች ሥርዓት-ምህዳር መልሶ ማቋቋም የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የማስፋጸሚያ ስልቶችን ይቀይሳል፣ አግባብ ባላቸው አካላት መተግበሩን ይከታተላል::

፰. የክልሉን ብዝሀ ህይወት ሀብት ተፈጥሮአዊና ሰውሰራሽ ቅርሶች፣ ፖርኮችና መጠለያዎች ጥበቃ፣ቁጥጥርና ክትትል የሚመለከቱ ጥናቶች ያካሂዳል፣ ተከልለዉ እንዲጠበቁና ተገቢ የአጠቃቀም ሥርዓት እንዲኖራቸዉ ሥልቶችን ይቀይሳል፣ ህጎችንና ደንቦችን ጸ□□ጽል፣ ሲፀዱቅም በሚመለከታቸው አካላት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል::ሰ

፱. የአካባቢ ሁኔታ ለማሻሻል አስተዋፅኦ ሊጸ□ርቶ በሚችል መልክ ማህበረሰቦች የየራሳቸውን የኃይል ፍላጎት ለማሟላት በአካባቢ ላይ የሚኖረዉን ተጽዕኖ ለማስቀረት እንዲችሉ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ጠቀሜታ ያላቸው ልምዶችን እና አሰራሮችን ያሰራጫል::

፲. አግባብ ባላቸው ህግጋት በተደነገገው መሰረት አካባቢን ከብክለት ለመጠበቅ ማናቸውም የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ በህብረተሰብ ተሳትፎና በተቆጣጣሪዎች አማካኝነት ክትትል ያካሂዳል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል::

፲፩. የከተማ ቆሻሻ /ጉድፍ/ አሰባሰብ፣ አጠቃቀም እና መልሶ መጠቀምና አወጋገድ የሰውን ጤናና የአካባቢን ደህንነት በማያቃውስ ሁኔታ መፈፀሙን ለዚህም ተገቢ መመሪዎችን አውጥቶ በስራ ላይ ያውላል::

፲፪. የክልሉን የአካባቢና የገጠር መሬት ሁኔታ ዘገባ ያዘጋጃል በየወቅቱ ለክልል መስተዳድር ምክር ቤትና ለፌደራል የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እንዲሁም ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል::

፲፫. ከፌደራሉ የመረጃ ማዕከሎች ሥርዓት ጋር በተጣጣመ መልኩ የክልሉ የአካባቢ ምጣኔ ሀብት የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ ጥናትና ትንተና ያካሂዳል፣ ያሰራጫል::

፲፬. የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ግንዛቤ በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲዳብር የአካባቢ ትምህርት በክልሉ የሚስፋፋበትን ስልት ይቀይሳል፣በትምህርት ካሪኩለም መካተታቸዉን ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፣ ትምህርት ይሰጣል፣ አስተማሪ የሆኑ ሞዴል የአካባቢ ልማት ስራዎች ያካሂዳል፣ እንዲሁም አርአያነት ያለው እንክብካቤ ሥራ □ሡሩ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና የሌሎች አካላት ተግባር በህዝቡ ዘንድ እንዲታወቅ ያደርጋል፣ የማበረታቻ ድጋፍ የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል አፈፃፀሙን ይከታተላል::

፲፭. በአካባቢ እንክብካቤ □ህብረተሰቡ ተሳትፎን ያበረታታል፣ እንዲጎለብትም ያደርጋል፡፡

፲፮. በክልሉ አካባቢን፣የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደርን በሚመለከቱ ጉዳዮች አግባብ ላላቸው አካላት ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፯. ለመሬት ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ወይም ድርጅቶች የይዞታና የመጠቀሚያ መሬት ትክክለኛ ስፋት በመወሰን በካርታ የተደገፈ ደብተር ለመስጠት የአሰራር ማንዋል በማዘጋጀት አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፲8. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን የመሬት ዓይነትና መጠን አጥንቶና መዝግቦ ይይዛል፣ያስተዳድራል፣ አጠቃቀሙን ይወስናል፣ ይቆጣጠራል፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል፣ እንደአስፈላጊነቱ መረጃዉን ለተጠቃሚዎች ይሰጣል፣

፲፱. መሬት በተለያዩ ምክንያቶች እንዳይጎሳቆል ወይም ምርታማነቱን እንዳያጣና ከጥቅም ውጭ እንዳይሆን የመሬት ተጠቃሚዎች በይዞታቸው ላይ የተለያዩ እንክብካቤዎች እንዲያደርጉ ትምህርት ይሰጣል፣ የማትጊያ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ግዴታቸውን በማይወጡ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣

፳. በመሬት የመጠቀም መብት የተሰጣቸው ግለሰቦች/ድርጅቶች/ የያዙትን መሬት የመጠቀም መብት በውርስ/በኪራይ/ የሚያስተላልፉበትን እና ሌሎች መሬትን ለማስተዳደር የሚወጡ መመሪያዎችና ደንቦችን ይቀርጻል፣ ሲፈቀድም ያስፈጽማል፣

፳፩. የግል ባለሃብቶች በመሬት ላይ የልማት ስራ ከመጀመራቸው በፊት የአጠቃቀም እቅዳቸውን እየገመገመ ያፀድቃል፣ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፡፡

፳፪. የክልሉን የአካባቢ፣ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር መረጃዎችን ለማደራጀት ስርዓት ይዘረጋል፣ ክልላዊ የመረጃ ቋት ይመሰርታል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ትንተና እያካሄደ ወቅታዊ ማስተካከያዎችን ያደርጋል፣ በአካባቢና በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ፍላጎት ላላቸው ተጠቃሚዎች ዝግጁ ያደርጋል ያሰራጫል፡፡

፳፫. የክልሉ የልማት ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ዘላቂ የመሬት አጠቃቀምን መሰረት አድርገዉ እንዲተገበሩ ክልል አቀፍ መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጃል፣

፳፬. የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅትን መሰረት ያደረገና የመሬት ተስማሚነት ደረጃን ግምት ዉስጥ በማስገባት የተስተካከለ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅት ላይና

በተሳትፎዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ አዘገጃጀት ላይ በየደረጃዉ ለሚገኙ ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፣ ይከታተላል፣

፳፫. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በህግ መሠረት ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡

፳፬. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣

፵፰. <u>ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት</u>

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት የሚከተሉ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

፩. የሀገሪቱን የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ፖሊሲዎች በክልሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፪. አሰሪና ሠራተኛን በሚመለከቱ የወጡ ደንቦች መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣

፫. ሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታዎች ደረጃቸውን የመከላከል ዘዴዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣

፬. ክልሉ የሚቋቋሙትን የሠራተኞችና የአሠሪ ማህበራትን ይመዘግባል ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣

፭. ህብረት ሥራ ድርድሮችና የሥራ ክርክሮች በህግ በተዘረጋው ሥርዓት ተከትለዉ ሥርዓት እንዲያገኙ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲፈጽሙ ጥረት ያደርጋል የህብረት ስምምነቶችንም ይመዘግባል፣

፮. በክልሉ ስለተሰማራው የሰው ሀይልና ባለመያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፣

፯. በክልሉ ሥራ ፈላጊዎች ክፍት የሥራ መደቦች እንዲመዘገቡና ሥራና ሠራተኛ እንዲገናኙ ለማድረግ የሚያስችል እርምጃዎችን ይወስዳል፣

፰. ለ ክልሉ የሠው ሀይል የሥራ ስምሪት ስለሠራተኞች ደህንነት ጤና እንዲሁም አሰሪና ሠራተኛ በሚመለከት ሌሎች ጉዳዮች መረጃዎችን ይሰበሰባል፤ ያጠናቅራል፤ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፣

፱. በተለያዩ ጡረታ ማህበራዊ ዋስትና ዕቅድ የሚሸፈኑ የክልሉ ሠራተኞች በመብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል እርምጃዎችን ይወስዳል፣

፲. አግባብ ካለላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አረጋዊያንና አካል ጉዳተኞችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ

ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፲፩. የማህበራዊ ጠንቆች እንዲወገዱ የክልሉን ህብረተሰብ ያስተባብራል አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፣

፲፪. የቤተሰብ ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የጋብቻ ሥርዓትን ለመከባከብ የሚወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

## ፳፱. የህዝብ አሰፋፈር፣ የምግብ ዋስትና፣ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ጽ/ቤት

የህዝብ አሰፋፈር፣ የምግብ ዋስትና፣ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ጽ/ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

፩ የገጠር ልማት ፖሊሲ፣የሀገሪቱን የምግብ ዋስትና ስትራተጅና ፕሮግራም መሠረት በማድረግ የክልሉ ህብረተሰብ አደጋን የሚቋቋም አቅም እንዲፈጥር በተጠኑ ቦታዎች ተሰብስቦ የማህበራዊ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፪ እስካሁን የተጠኑ ጥናቶችንና የተዘጋጀውን የምግብ ዋስትና እስትራቴጂ ፕሮግራም ዶክሜንት መሠረት በማድረግ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ሀብት የማፈላለግ ሥራ ይሠራል፣

፫ በክልሉ አደጋ በተከሰተ ጊዜ የደረሰውን ጉዳትና መወሰድ የሚገባውን እርምጃ የሚያስፈልገውን ድጋፍ በዝርዝር የሚያመላክት ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡

፬ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር አደጋን ለመከላከል የተቀየሱ ፖሊሲዎችና ሥልቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

፭ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን እና ከሌሎች ምንጮች ለክልሉ የተደለደለውን ዕርዳታ ለተረጂዎች መድረሱን ያረጋግጣል፣

፮ ለዕርዳታ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ ልማት ነክ ፕሮጀክቶችን ዝግጅትና አፈጻጸም ያስተባብራል፣

፯ በተለያዩ ምክንያት የምግብ እጥረት ያጋጠማቸው የክልሉ አካባቢዎች በዘላቂነት መፍትሔ ሊሆን የሚችል ሥልቶችን፣ ፕሮግራሞችን ፕሮጀክቶችን ከጥናት ጀምሮ እስከሚፈጸሙ ድረስ በባለቤትነት ይሠራል፣ ሌሎችንም ለሥራው ያስተባብራል፡፡

፰ የሕብረተሰቡን፣የለጋሽ ድርጅቶችን የመንግስት አቅምና ድጋፍ በማጣጣም ለምግብ ዋስትና መረጋገጥ ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይሠራል፡፡

፱ ለምግብ ዋስትና የሚገኙ የተለያዩ የሀብት ምንጮችን ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በአግባቡ ያሠራጫል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ለለጋሾችም ሆነ ለመንግስት የሥራውን ሂደትም ሆነ የፋይናንስ ሪፖርት በወቅቱ ያቀርባል፡፡

፲. የመሠረተ ልማት ተቋማት ሕብረተሰቡ በመንደር በሚሠባሰብባቸው አካባቢም እንዲሟሉ ከሚመለከተቸው ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡

፲፩. የክልሉን ቀደምት ኗሪዎች አኗኗር ያጠናል፣ ቀደምት ኗሪዎች በፈቃደኝነት በመንደር በማሰባሰብ ለመኖሪያ ምቹ የሆኑ ቦታዎችን ይመርጣል፣

፲፪. የቁጠባ ባህል በማዳበር ለፍጆታ፣ ለገበያ፣ ለዘርና ለመጠባበቂ የእህል ምርት ሕብረተሰቡ እንዲይዝ ያበረታታል፣ ምክርና እገዛም ይሰጣል፣

፲፫. የጽ/ቤቱን የአጭር፣ የካከለኛና እና የረጅም ጊዜ እቅዶችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ይተገብራል፣

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፴. ስለሌሎች አስፈጻሚ አካላት

በዚህ አዋጅ ውስጥ ሥልጣንና ኃላፊነታቸው ያልተገለጸ የክልሉ አስፈጻሚ አካላትና ሌሎች ተቋማት ሥልጣንና ተግባር በተቋቋቀሙበት አዋጅ ወይም ደንብ በተደነገገው መሠረት የተገለጸው ይሆናል፡፡

### ፴፩. የአስፈጻሚ አካላት ቅርንጫፎች በየደረጃው የሚቋቋሙ ስለመሆኑ፣

የክልል መስተዳድር ም/ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ አስፈጻሚ አካላትን በክልሉ ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው ሊያደራጅ ይችላል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

### ፴፪. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸዉ ሕጐች

0 ከዚህ በፊት በክለሉ መንግሰት ምክር ቤት የወጡ የሚከተሉት አዋጆች በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

ሀ. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋምና ስልጣንና ተጋባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫/፲፱፻፹፰፣

ለ. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የውሃ፣ የማዕድንና ኢነርጅ ሀብት ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፪/፲፱፻፺፫፣

ሐ. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፫/፲፱፻፺፫፣

መ. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን

የወጣ አዋጅ ቁጥር ፴፬/፲፱፻፺፫፣

ሠ. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አደረጃጀት ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር #፪/፲፱፻፺፫፣

ረ. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ስልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን የወጣ የማሻሻያ አዋጅ ቁጥር $፯/፲፱፻፺፫፡፡

1 ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛዉም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ዉስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፴፫. <u>**መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**</u>

፩ በአዋጅ ቁጥር $፯/፲፱፻፺፫ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ተቋቁመው የነበረዉ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ እና የንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመዉ የንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርትና ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተላልፏል፡፡

፪ በአዋጅ ቁጥር ፳፫/፲፱፻፺፫ መሠረት ተቋቁሞ የነበረው የማስታወቂያ፣ ባህል፣ ቱሪዝምና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ መብትና ግዴታዎች እንደየአግባብነታቸዉ በዚህ አዋጅ ለተቋቋሙት የመንግስት ኮሙኒዩኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ወይም የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ወይም ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ይተላለፋል፡፡

፫ በአዋጅ ቁጥር $፯/፲፱፻፺፫ መሠረት ተቋቁሞ የነበረዉ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ መብትና ግዴታዎች እንደየአግባብነታቸዉ በዚህ አዋጅ ለተቋቋሙት የስፖርት ኮሚሽን ወይም የሴቶች፣ ወጣቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ይተላለፋል፡፡

፬ በአዋጅ ቁጥር $፯/፲፱፻፺፫ መሠረት ተቋቁሞ የነበረው አቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ የሲቪል ሰርቪስ ቢሮና ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመዉ የአቅም ግንባታና ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ተላልፏል፡፡

፴፬. <u>**ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን**</u>

ሀ. የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

ለ. የአስፈጻሚ አካላት ይህንን አዋጅና ተከትሎ የሚወጡ ደንቦችን

ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪዎችን ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

**፩5. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አሶሳ መስከረም ፲፰ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም**

**አህመድ ናስር አህመድ**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**

**ፕሬዚዳንት**